# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የስብከት ዘመን አንደኛ ሰንበት

ከታህሣሥ ፯ ቀን ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ፳፰ ቀን ያለው ዘመን ዘመነ ስብከት ይባላል። ምክንያቱም ነቢያት የጌታን በሥጋ መምጣት አምልው አስፍተው በትንቢት በትምህርት በማስተማር መስበካቸውን ቤተ ክርስቲያን እያሰበች ሰውን ለማዳን ወደ ምድር የመጣውን አምላክ የምትሰብክበት ወቅት በመሆኑ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ፈኑ እዴከ እምአርያም
አድኅነኒ ወባልሐኒ እማይ ብዙኅ
ወእምእዴሆሙ ለደቂቀ ነኪር

እጅህን ከአርያም ላክ አድነኝም
ብዙ ውኆች አፋቸውም ምናምናና ከሚናገር አድነኝ

መዝ ፩፻፵፫፥፯

ምስጢር (ትርጉም)፦ ልጅህን (ክንድህን) ከአርያም ልኮ በልጅህም (ከውኆች) ከፍትወታት እኩያት በኃጢአት ከፍዳ ከመከራ ነፍስ አድነኝ (ምናምን ከሚናገሩ) ከዲያቢሎስ ወገኖች ስልጣን አድነኝ ማለት ነው።

ወንጌል፦ ዮሐ ፩፥፵፬ እስከ ፍጻሜ
ቅዳሴ፦ የአትናቴዎስ ቅዳሴ

ይህ ዕለት ሰብከት ይባላል። በዚህ ዕለት በኦሪተ ሙሴ፣ በነቢያት፣ በመዝሙራት አስቀድሞ ስለ ክርስቶስ ሥጋዌ (ሰው መሆን፣ ሥጋ መልበስ) ትንቢት ተናግሮ፣ ምሳሌ አስመስሎ፣ ሱባኤ ተቆጥሮ እንደነበር ይናገራል ይሰበካል። ስለዚህ ነቢያቱ መምጣቱን አስቀድመው ሰብከው ነበር ለማለት ስብከት ተባለ።

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፩፥፩ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፪ኛ ጴጥ ፫፥፩-፲ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፫፥፲፯ እስከ ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# መድኃኒት ልጁን እንሰብካለን

በሙሴ አሪት በነቢያት በመዝሙራት መድኃኒት ልጁ ተሰብኮ ነበር። መድኃኒት የሚል ስም ያለው ኢሳይያስ ከድንግል ስለመወለዱ ሰበከ (ኢሳ ፯፥፲፬ ። ማቴ ፩፥፳፫)።

ማን እግዚአብሔር የተባለው ሚክያስም በቤተ ልሔም እንደሚወለድ ሰበከ (ሚክ ፭፥፪ ። ማቴ ፪፥፮) ነቢዩ ሆሴዕም ቀዳማዊ አዳምን ወደቀደመ ክብሩ ለመመለስ ወደ ግብጽ እንደሚሰደድ ሰበከ (ሆሴዕ ፲፩፥፩ ። ማቴ ፪፥፲፭)። በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን እንደሚያዩ በመጋዝ የተተረተረው ነቢይ ሰበከ (ኢሳ ፱፥፩-፪ ። ማቴ ፬፥፲፮) በተቀጠቀጠ መቃ እና ብርሃኑ በጠፋ ጧፍ የተመሰለው የሰው ሕይወትም እንደማይጠፋበት ሰበከ (ኢሳ ፵፪፥፩-፬ ። ፲፪፥፲፰)። ስለሚያስተምረው ወንጌል፤ ስለሕዝቡ አቀባበል ሰበከ (ኢሳ ፮፥፱-፲ ። ማቴ ፲፫፥፲፬)። (ኢሳ ፳፱፥፲፫ ። ማቴ ፲፭፥፰-፱) የትምህርቱ በምሳሌ መሰበክም በነቢያት ትንቢት አልተረሳም (መዝ ፸፯፥፪ ። ማቴ ፲፫፥፴፬-፴፭) የሆሳዕና ጉዞው (ዘካ ፱፥፱ ። ማቴ ፳፩፥፭) በፈሪሳውያን ስለመናቁ፤ እርሱም የማዕዘን ድንጋይ መሆኑ (መዝ ፩፻፲፯፥፳፪-፳፫ ። ኢሳ ፳፰፥፲፮ ። ዳን ፪፥፴፬-፵፭ ። ማቴ ፳፩፥፵፪) የሚወለደው እግዚአ ዳዊት አምላከ ዳዊት ስለማባሉ (መዝ ፩፻፱፥፩ ። ማቴ ፳፪፥፵፬) ለሰላሳ ብር መሸጡ (ኤር ፲፰፥፲፪ ። ዘካ ፲፩፥፲፪ ። ማቴ ፳፯፥፱) ለድሆች ወንጌልን፤ ለታሰሩ መፈታትን፤ ለእውሮች ማየትን፤ ለተጠቁ ነጻነትን ለመስበኩ ተሰብኳል። (ኢሳ ፷፩፥፩-፪ ። ሉቃ ፬፥፲፯-፳፩) በጉባኤ ተፈርዶበት እጆቹ እግሮቹ ተቸንክረው መሰቀሉን፣ መራራ ሐሞት መጠጣቱን፣ ልብሱን ወታደሮች መከፋፈላቸውን (መዝ ፳፩፥፩-፳፩ ። ዮሐ ፲፱፥፳፫-፳፬ ። ዮሐ ፲፱፥፳፱-፴)። ዘማሪው ዘምሮአል፣ መቁሰሉን፣ መከራውን መቃብሩም ከክፉዎች ጋር መሆኑን ነቢዩ ሰበከ (ኢሳ ፶፫፥፩-፲፪ ። ፩ኛ ጴጥ ፪፥፳፩-፳፭)፤ ከሙታን መነሳቱን (መዝ ፲፭፥፲፭ ። ማቴ ፳፰)፤ ወደ ሰማይ ማረጉን (መዝ ፷፯፥፲፰ ። ማር ፲፮፥፲፮-፲፰)፤ በሥጋ ካረገ በኋላም ዳግም መምጣቱን ሳይቀር ነቢያት ሰብከዋል (መዝ ፵፱ ። የሐዋ ሥራ ፩፥፱-፲፩። ከዚህ በላይ እንዳየነው በነቢያት መድኃኒት ልጁ በሰፊው ተሰብኳል። በዕብራውያን መልእክት እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢያት ለአባቶቻችን በኋላም ለእኛም በመጨረሻው እንደነገረን ተጽፏል። በወንጌሉም በሕዝበ እስራኤል እነዚህ ሁሉ የክርስቶስን መድሕንነት የሚያስገነዝቡ ናቸው።

አንባቢ ሆይ፦ መሲህ በነቢያት እንደተሰበከ አነበቡ፤ ለእርስዎስ ዛሬ ማን ይሰብክልዎታል? ማንንስ ይሰንካሉ? ቅዱስ ጳውሎስ «ንህነሰ ንሰብክ ክርስቶስሃ ዘተሰቅለ - እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን» ይላል። አዎን መሰበክ ስለሚገባው ወንጌሉም ስለማያሳፍር ነው። እርስዎም ለሰዎች ሊነግሩት ከጓደኞችዎ ጋር ሊነጋገሩበት የሚገባ የሕይወት ዜና ክርስቶስ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በጊዜውም አለጊዜውም ሲሞላም ሲጎድልም እንድንሰብከው ያዛል። ስለዚህ መቼም መች ስለኃጢአታችን የሞተውንና ብቻውን መድኃኒት የሆነውን ልንሰብክ ይገባል። (፪ኛ ጢሞ ፬፥፪-፭ ። ሮሜ ፩፥፲፭-፲፯ ። ፪ኛ ቆሮ ፬፥፭-፮)።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።